# መመሪያ/ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS – ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** IKA, IKA-RA, IKB-RA, IKC-RA, IOE-RA, JFA, JFA-RA, JGA-RB, KLA, KLA-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** Office of the Chief of Teaching, Learning and Schools

## የተማሪ ክትትል

I. **ዓላማ**

በሜሪላንድ ደንብ ኮድ ላይ በተገለጸው መሠረት ከትምህርት መቅረትን እና በምክንያት ፈቃድ አግኝቶ መቅረትን የመመዝገብ ኃላፊነት ለመስጠትና ከተማሪዎች እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር መቅረትን ለመቆጣጠርና የሚሻሻልበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ Code of Maryland Regulations (COMAR)

II. **ቅደም-ተከተል**

A. ሁሉም ት/ቤቶች

1. ቀሪዎችን መመዝገብ

a) እያንዳንዱ የክፍል አስተማሪ የተማሪዎችን ክትትል የመመዝገብ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። መምህራን የተማሪዎችን መገኘት/አለመገኘት በቀጥታ በኦንላይን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ይመዘግባሉ። ሲስተሙ የተመዘገበበትን ቀን፣ ሠዓት፣ እና መረጃ መዝጋቢውን ሰው ይገልጻል።

b) የኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ለመጠቀም በማይቻልበት ሁኔታ፣ የወረቀት ሮስተር/መዝገብ መጠቀም ይቻላል። እነኚህ መረጃዎች/ዶኩሜንቶች የትምህርት ዓመቱ እስከሚያልቅ በት/ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ። የትምህርት ወቅቱ ሲጠናቀቅ፣ በመዝገብ ያሉት መረጃዎች/ዶኩመንቶች ወደ ማእከላዊ መዝገብ ቤት ተልከው ኦዲት ለማድረግ ካስፈለገ በተጨማሪ ለሦስት ዓመት ይቀመጣሉ።

c) በየቀኑ ተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት/አለመገኘት በኤሌክትሮኒክስ እየተመዘገበ በቴክኖሎጂ ዋና ኦፊሰር ጽ/ቤት ይቀመጣል። የተማሪ ትምህርት የመከታተል ሁኔታ በየእለቱ ያለው ሪኮርድ የአመቱ ተጠራቅሞ በቋሚ መዝገብ ላይ ማዕከላዊ የተማሪ መረጃ ቋት ላይ ለሦስት ዓመት ይቀመጣል።

2. ከት/ቤት መቅረት ጋር የተያያዙ መንስኤዎችን ማረጋገጥ

a) ለሪፖርት አቀራረብ እንዲያመች፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሜሪላንድ የተማሪ ሪኮርድ ሲስተም መምሪያ ትምህርት ላይ አለመገኘትን "የቀረባቸው/የቀረችባቸው ቀኖች" በማለት ይገለጻል።

b) የሚሬላንድ የተማሪ ሪኮርድ አያያዝ መምሪያ በማጣቀሻነት ከዚህ ጋር አባሪ ተደርጓል።

3. ከትምህርት የቀረ(ች)በት ሁኔታ ህጋዊ መሆኑን ወይም ህጋዊ አለመሆኑን ማረጋገጥ

a) ተማሪው(ዋ) ወደ ት/ቤት በተመለሰ(ች) በሦስት ቀን ውስጥ ከወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ የቀረ(ች)በትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። "ብቁ ተማሪ/Eligible student" ምን ማለት እንደሆነ በ MCPS Regulation JEA-RB ላይ ተገልጿል፣ ስለ ተማሪዎች ምዝገባ/Enrollment of Students

b) አርፍዶ ስለመምጣት ወይም ቀደም ብሎ የመውጣት ፈቃድ ለመጠየቅ በወላጅ/ሞግዚት መረጋገጥ አለበት።

c) ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ስለመቅረት ማስታወሻ ማቅረብ እና አርፍዶ ስለመምጣት እንዲሁም በትምህርት ሠዓት ቀድሞ ስለመውጣት ጉዳይ ኃላፊነት መውሰድ ይኖርበ(ባ)ታል። ርእሰመምህር/ተወካይ ብቁ ስለሆነ(ች) ተማሪ የሚከተለውን በጽሑፍ ለወላጅ/አሳዳጊ የመግለጽ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

(1) ብቃት ያላቸው ተማሪዎች የቀሩበትን ምክንያት ራሳቸው በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላሉ።

(2) እድሜው(ዋ) የሚፈቅድ ተማሪ ላይም ሕገ-ወጥ ከትምህርት የመቅረት ሁኔታን አስተዳደራዊ ክትትል ይደረጋል። በተጨማሪ ተማሪው(ዋ) ከወላጅ/ሞግዚት ጋር በጥገኝነት የሚኖር/የምትኖር ከሆነ ሳይፈቀድ የመቅረቱ(ቷ) ሁኔታ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ይገለጻል።

d) በፐብሊክ ስኩልስ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ምንም ያህል ሠዓት ቢሆን ከት/ቤት መቅረታቸው እንደህጋዊ መቅረት/ማርፈድ ሊቆጠር የሚችለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ነው፡- [1]

(1) በት/ቤት፣ በአካባቢ የትምህርት ሥርዓት፣ ወይም በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ሊያስቀራቸው የሚችል መሆኑን በአካባቢ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም በት/ቤት ርእሰመምህር/ተወካይ ተቀባይነት ያለው የጸደቀ ወይም የተፈቀደ ሥራ። ርእሰመምህር/ተወካይ ህጋዊ አድርጎ መቀበል ያለበት የእንቅስቃሴ ብዛት ወይም የሥራ መጠን ምክንያት ከአምስት የትምህርት ቀናት አስቀድሞ ተማሪው(ዋ) ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው ተማሪ በጽሑፍ ከተጠየቀ እንደሚከተለው ይሆናል።

(a) ኮሌጅ ለመጎብኘት እና በኮሌጅ የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞች ለመሳተፍ (ለምን ያህል ጊዜ እንደሚፈቀድ ከአካባቢ የተማሪ መመሪያ መጽሔት ይመልከቱ)

(b) ከወደፊት ቀጣሪዎች ጋር ለቃለ መጠይቅ የተያዘ ቀጠሮ

(c) በቅንጅት የመማር ፕሮግራም ያልተመዘገቡና የአጭር ጊዜ ሙሉ-

---

[1] □□□ □□□ □□□□□□ □□□□□□□/□□□□□ □□□□□□□□ □□□□□□

ጊዜ ሥራ ለተመደቡ ተማሪዎች

(2) በቅርብ ቤተሰብ መሞት ምክንያት

(3) የተማሪ ህመም እና ደህንነት ስጋቶች
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በትምህርት ላይ በብቃት መሳተፍ እንዲችሉ አካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባል። በህመም፣ አካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ደህንነትን በሚደግፉ ተግባራት ለመሳተፍ የተማሪ መቅረትን ትምህርት ቤቶች በፈቃድ እንደመቅረት ይቀበላሉ።

(i) በዚህ ደንብ መሰረት ከደኅንነት ተግባር ጋር የተያያዘ የተማሪ መቅረት ተመልሶ ትምህርት ማግኘት እንዲችል/እንድትችል አወንታዊ የአካል እና/ወይም የአእምሮ ጤንነትን የሚደግፉ ፕሮግራሞች ወይም ቴክኒኮች ተደርገው ይወሰዳሉ።

(ii) አንድ ተማሪ ሥር የሰደደ ወይም ለተራዘመ ጊዜ የቀረ(ች) ከሆነ፣ ርእሰ መምህሩ(ሯ) የተማሪን ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ፈቃድ ካለው የጤና እንክብካቤ ሰጪ የቀረ(ች)በትን ምክንያት የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ/እንድታቀርብ መጠየቅ ይችላል። ከጤና ባለሙያ የተሰጠ ሰነድ ከሌለ ቤተሰብን የሚረዱ የማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች ወይም ለረዥም ጊዜ የተማሪን መቅረት የሚያውቁ የት/ቤት ሰራተኞች በስነ-ልቦና ደህንነት ምክንያት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ መስጠት ይችላሉ።

(4) እርግዝና - ወይም ከወሊድ/ከወላጅነት ጋር የሚገናኙ ሁኔታዎች

(a) ት/ቤቶች የተማሪን መቅረት ምክንያታዊ እንደሆነ የሚቀበሉት፦ በእርግዝና ምክንያት ወይም ከወሊድ-ጋር በተያያዙ ምክንያቶች (ምጥ፣ መውለድ፣ አራስነት፣ እና ከወሊድ በፊት እና ከወሊድ በኋላ ለህክምና ቀጠሮዎች የሚቀሩትን ተማሪዎች፣ ት/ቤቶች ምክንያታዊ እንደሆነ ይቀበላሉ

(i) ተማሪ ልጅ ከወለደች በኋላ ቢያንስ ለ 10 ቀናት የመቅረት የወሊድ ፈቃድ ይኖራታል፣

(ii) በተማሪው(ዋ) ህጻን መታመም ወይም በህጻን የህክምና ቀጠሮ ምክንያት በአራስነት ያለ(ች) ወላጅ ከትምህርት ቤት መቅረት፣ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ የሃኪም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ከሚሰጠው የአራት ቀን ከት/ቤት መቅረት ጭምር የሃኪም ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልገውም።

(iii) በእርግዝና ወይም በወላጅነት ምክንያት ወይም ከቤተሰብ ህግጋት ጋር የሚገናኝ፣ ጉዲፈቻን ጨምሮ፣ የልጅ አሳዳጊነት እና ጉብኝት ማናቸውም ህጋዊነት ባለው ቀጠሮ

ምክንያት መቅረት

(b) አንዲት ተማሪ በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያት ሆስፒታል ከገባች ፈቃድ ካለው የህክምና አገልግሎት ሰጪ ማስረጃ መጠየቅ ያለባቸው፣ሌሎች ተማሪዎችም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ሆስፒታል ሲገቡ የሃኪም ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ ከሆነ ብቻ ነው።

(5) ከፍርድ ቤት የመጥሪያ ትዕዛዞች

(6) ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ ሲጓዝ/ስትጓዝ የጤንነት አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ዓይነት ከባድ የአየር ጠባይ/ሁኔታ

ኃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለማክበር

(8) ድንገተኛ ሁኔታ

(9) መባረር/መታገድ

(10) በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ግምት ከትምህርት ቤት ለመቅረት በቂ/አሳማኝ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ ሌሎች አስቸኳይ/አጣዳፊ ምክንያቶችና ሁኔታዎች

(11) የመጓጓዣ አገልግሎት እንዲሰጣቸው የተፈቀዳላቸውን ተማሪዎች ከ MCPS የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጥ የሚያግዱ/የሚከለክሉ ሁኔታዎች በዲስፕሊን ቅጣት ምክንያት ከ MCPS የመጓጓዣ አገልግሎት መታገድን አይጨምርም

e) ማናቸውም ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ውጪ በሆኑ ምክንያቶች መቅረት በርእሰመምህር/ተወካይ ህጋዊ ሊሆን ወይም ህጋዊ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። እላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጪ የሆኑትን መቅረቶች እንደ ህጋዊ አድርጎ የመቀበል ስልጣን የተፈቀደ ነው። እንደአግባቡ ለቤተሰብ ጉዞ ፈቃድ መጠየቅ እንደህጋዊ መቅረት አይቆጠርም።

በርእሰመምህር/ተወካይ ውሳኔ የተማሪ መቅረት ህጋዊ ተደርጎ ሊቆጠር የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ተመስርቶ መሆን አለበት።

(1) በተማሪው(ዋ) መቅረት ምክንያት በትምህርቱ(ቷ) ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቀነስ የማካካሻ ሥራ ሊኖር እንደሚችል የተማሪን የመቅረት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከተማሪው(ዋ) መምህር/መምህራን አስተያየት ከተሰጠ

(2) በተማሪው(ዋ) ላይ የተጠራቀመ ህጋዊ የሆኑና ህጋዊ ያልሆኑ በቀሪነት የተመዘገቡ ቀኖች ቁጥር

(3) መቅረት ያስፈለገበት ዓላማ ወይም ልዩ ምክንያት

(4) የቀረ(ች)በት ጊዜ ብዛት

f) አስፈቅዶ ለመቅረት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከት/ቤት ስለመቅረት ጥያቄ ማስታወሻ መቅረብ ይኖርበታል።

g) ተማሪ በአካል መማሪያ ክፍል በማይገኝበት ጊዜ፣ ነገር ግን በ MCPS ቀጥታ ቁጥጥር እስከተደረገ ድረስ በስቴት እና በአካባቢ ሪፖርት በማድረግ ተማሪዎች እንደተገኙ ተደርጎ ይቆጠራል፣ ቢሆንም ግን በመማሪያ ክፍል ውስጥ አለመገኘታቸውን ለማረጋገጥ በመምህር አማካይነት ቀሪ ተብሎ ይመዘገባል። በስቴት እና በአካባቢ ሪፖርቶች ላይ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ እንዲረዳ የቀሪ ተቆጣጣሪ ጸሐፊ ተግባራዊ የሆነ መለያ ኮድ ይመድባል/ትመድባለች። ይህን የመሳሰለ የመቅረት ምሳሌዎች፣ በዚህ ብቻ አይወሰንም፡-

(1) በ MCPS የመስክ ትምህርት ፕሮግራሞች በበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት መስጠት

(2) የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአትሌቲክስ ተሳትፎ

(3) የተማሪ አስተዳደር

(4) የመስክ ጉዞ

(5) የጤና አገልግሎት ክፍል ጉብኝት

(6) መካከለኛ/መሸጋገሪያ የትምህርት አገልግሎቶች

(7) ከት/ቤት መታገድ

h) በረዥም ጊዜ ጉዞ ምክንያት ወይም ምክንያቱ ሳይገለጽ ከ 15 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት ከት/ቤት የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት መልቀቅ ይኖርባቸዋል፣ እና ተማሪው(ዋ) ከት/ቤት መልቀቅ እንዳለበ(ባ)ት ለወላጅ/ሞግዚት ይገለጻል። MCPS የሚገምተው ወላጅ/ሞግዚት ተማሪው(ዋ) ከደረሰበት ደረጃ ትምህርት የማስቀጠል ኃላፊነታቸውን እንደሚያሟሉ ተደርጎ ይታሰባል።

i) ፍጹም ለተሟላ የትምህርት መከታተል ት/ቤት ሽልማት ለመስጠት ከፈለገ፣ በኃይማኖታዊ ምክንያት ከት/ቤት እንዲቀሩ የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች ከተሸላሚነት አያግድም።

4. ከትምህርት መቅረትን መቆጣጠር

a) ተማሪው(ዋ) የቀረ(ች)ባቸው ቀኖች በጠቅላላ (በፈቃድ የሆኑትና ያለፈቃድ የቀረ(ች)ባቸው) በሪፖርት ካርድ ላይ ሪፖርት ይገለጻሉ።

b) ርእሰመምህር/ተወካይ ከት/ቤት ባልደረቦች ጋር በመተባበር፣ ከት/ቤት ስለመቅረት ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት በመመስረት በየዓመቱ ጁላይ 1 ላይ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው የት/ቤቶች ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ያቀርባል፣ እና ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ የጸደቀውን የመቆጣጠሪያ ሥርአት ይሰጣቸዋል።

c) የተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ጽ/ቤት ከሌሎች የ MCPS ጽ/ቤቶች እና የውጭ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር መደበኛ የትምህርት ክትትል ሳይጓደል ለመከታተል የሚያስችል ጣልቃገብነት ስልት በማዳበር ተግባራዊ ያደርጋል።

d) እያንዳንዱ ት/ቤት የራሱን የቀሪዎችን መቆጣጠሪያ ስልት ያበጃል። ይህም ስልት መረጃዎችን ይቆጣጠራል፣ የትኩረት ጣልቃገብነትን ያመለክታል፣ እና ማበረታቻዎችን ያካትታል።

B. አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ሙዓለ ህጻናትን ይጨምራል)

1. በትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ርእሰመምህራን/ተወካዮች ልጃቸው በማንኛውም ቀን በምንም ምክንያት ከት/ቤት የሚቀር/የምትቀር ከሆነ ለት/ቤት እንዲያሳውቁ ወላጆችን/ተወካዮችን ይጠይቃል/ተጠይቃለች።

2. በተቻለ መጠን፣ በኤለመንተሪ ትምህርት/ቤት እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ከት/ቤት እንደሚቀሩ አስቀድመው ካላሳወቁ በስተቀር በ 12፡00 ሠዓት እኩለ ቀን ላይ በእያንዳንዱ መጀመሪያ በሚቀሩበት ቀን ይነገራቸዋል።

3. በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የኤለመንተሪ ት/ቤት ተማሪዎች እና/ወይም አርፋጆች አግባብነት ወዳለው ጣልቃ የመግባት ትግበራ እንዲተላለፉ ሊደረግ ይችላል። በርእሰምምህሩ/በርእሰምምህሯ ወይም በእርሱ/ በእርሷ ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌላ ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ።

C. መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች

በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና/ወይም አርፋጆች አግባብነት ወዳለው ጣልቃገብ እንዲያመሩ ሊደረግ ይችላል። በርእሰመምህሩ(ሯ) ወይም በእርሱ(ሷ) ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ። አምስት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ት/ቤት ቀሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል።

D. ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

1. ተማሪዎች ያለበቂ ምክንያት የሚያረፍዱ ከሆነ እየተመዘገበ ሦስት ጊዜ ያለምክንያት ካረፈዱ አንድ ቀን ያለፈቃድ እንደቀሩ ተደርጎ ይቆጠራል።
2. ሦስት ጊዜ ያለፈቃድ ከክፍል የሚቀሩ ተማሪዎች ኮርስ ወዳቂዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይችላል እናም ወደ ትምህርት ቤት ካውንስለር እና ወደ ርእሰመምህር ይላካሉ። የት/ቤት ካውንስለር ተማሪው(ዋ) የቀረ(ች)በትን ምክንያት ለማረጋገጥ እና ተገቢ የሆነ ጣልቃገብ እርምጃ ለመወሰን ከተማሪው(ዋ) እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ምክክር ያደርጋል/ታደርጋለች።

3. ከትምህርት ክፍል አምስት ቀን ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ወይም ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው

ስለተመዘገበባቸው የመቅረት ሪኮርድ ትክክለኛነት ጥርጣሬ ካላቸው ይግባኝ እንዲያመለክቱ ይገለጽላቸዋል፣ ወይም በትምህርት ቤታቸው ካውንስል/ርእሰመምህር አማካይነት የመከታተል ጣልቃገብ-እርምጃ እቅድ/attendance intervention plan ይዘጋጃል።

ስለመቅረት አመዘጋገብ ይግባኝ ጥያቄ በተማሪ/ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው(ያላት) ተማሪ፣ ወይም በትምህርት ቤት ካውንስለር/የአስተዳደር ቡድን፣ አማካይነት MCPS Form 560-26A ቅጽ በመጠቀም ሊቀርብ ይችላል፣ ት/ቤት የመገኘት-የመከታተል ምዝገባ፣ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ/Appeal of Attendance Recording, High School Students Only።

4. የትምህርት ቤት ካውንስለሮች/የአስተዳደር ቡድኖች ትምህርት ቤት የመከታተል-የመሳተፍ ጣልቃ ገብ እቅድን/Attendance Intervention Plan (AIP) ለተማሪ ትምህርት የመከታተል ማሻሻያ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

   a) እያንዳንዱ ተማሪ ስለሚወስዳቸው ኮርሶች MCPS Form 560-26B ቅጽ በመጠቀም የሚዘጋጀው ትምህርት የመከታተል-የመሳተፍ ጣልቃ ገብ እቅድ/Attendance Intervention Plan (AIP)፣ የመከታተል-የመሣተፍ እቅድ፣ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ/Attendance Intervention Plan, High School Students Only የተማሪን የትምህርት ክትትል እና አካደሚያዊ ሥራ ስለማሻሻል ተማሪው(ዋ) እና/ወይም ሠራተኛ አማካይነት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና ስትራቴጂዎች በቅጹ/ፎርሙ ላይ ተቀምጠዋል።

   b) ርእሰመምህር AIP ከመረመረ(ች) በኋላ ይፈርምበታል/ትፈርምበታለች።

   c) AIP ተግባራዊ እየተደረገ እያለ፣ ሴሚስተሩን በሙሉ ተማሪ መከታተሉ(ሏ)ን እና AIP ያስከተለውን ውጤት ርእሰመምህር ግምገማውን ይመራል/ትመራለች።

   d) አንድ ተማሪ አምስት ጊዜ ወይም ከዚያ የበለጠ መቅረቶች ካሉበ(ባ)ት፣ እና በ AIP ጣልቃገብ ምክንያት ተማሪው(ዋ) ማሻሻያ አለማሳየቱ(ቷ)ን የትምህርት ቤት ቡድን ከወሰነ፣ ተማሪው(ዋ) በዚያ ኮርስ የወደቀ(ች)በት ውጤት ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

   e) ማለፊያ ውጤት ማግኘት እየቻሉ ነገር ግን ትምህርት ባለመከታተል ምክንያት የመውደቅ ውጤት ላገኙ ተማሪዎች፣ ርእሰ መምህሩ(ሯ) ለተማሪው(ዋ) ማለፊያ ውጤት ለማግኘት የሚችልበትን-የምትችልበትን ሂደት ያስጀምራል/ታስጀምራለች።

5. የመውደቂያ ውጤት ይግባኝ መጠየቅ የሚቻለው በቦርድ ፖሊሲ "Board Policy KLA" መሠረት ይሆናል Responding to Inquiries and Complaints from the Public/ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ ስለመስጠት።

6. በ MCPS ደንብ KLA-RA ላይ የተቀመጡት መደበኛ እርምጃዎች፣ለሕዝብ ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች ምላሽ መስጠት፣ ቅሬታዎችን ለመፍታት በአከባቢው ት/ቤት ይፋ ባልሆነ አቀራረብ ቅሬታውን ለመፍታት ካልተሳካ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

***ተዛማጅ ምንጮች:-*** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-301.1; Code of Maryland Regulations §13A.03.02.08B(4) and §13A.08.01.01–07; MCPS Guidelines for Respecting Religious Diversity; A Student's Guide to Rights and Responsibilities; Student Code of Conduct in Montgomery County Public Schools

**የደንቡ ታሪክ፡-** የቀድሞው ደንብ ቁጥር 515-1፣ ሴፕቴምበር 12፣ 1980 (የማውጫው መረጃ ተሻሽሏል)፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል። ኦክቶበር 28/1993 ተሻሽሏል። ኦገስት 19/1997 ተሻሽሏል፣ኖቨምበር 3 ቀን 2005 ተሻሽሏል፣ሜይ 12 ቀን 2010 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 7/2013 ተሻሽሏል፣ ፌብሩዋሪ 4/2014 ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 11/2014 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 6/2015 ተሻሽሏል፣ፌብሩዋሪ 9/2018 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 8/2019 ተሻሽሏል፤ ኖቨምበር 3/2021 ተሻሽሏል።